September 10, 2011
Dallas , USA

# ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ምንድን ነው ?

ዶ/ር አክሎግ ቢራራ

## ሀ. የስምምነት መስኩ ምን ይመሳላል ?

ሁሉም ፥መልካም አስተዳደር ፥የሕግ የበላይነት፥ፍትኅ-ርትዕ፥ ሰብዓዊ መብቶች፥ ነፃነት፥ እኩልነት፥ ተሳትፎና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ይፈልጋል ::

## ለ. ችግሩስ ምንድን ነው?

በአጭሩ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና ለሀገራችን ዘላቂ ጥቅም የምንሻው ራዕይ ጉዳይ ነው:: በአለፉት አርባ ዓመታት የፖለቲካ ተዋናውያንና ደገፊዎቻቸው ያተኮሩት በሚያስማሙና በሚያቀራርቡ ዓበይት ጉዳዮች ሳይሆን፥ በልዩነታቸው ላይ ነበር :: አገራዊና ኢትዮጵያዊ መፍተሄ አስፈላጊ ሲሆን፥ በጎሳ የተመሰረተ የፖለቲካና ከአንዳንድ አካባቢዎች የመነጨ የቅኝ አገዛዝ ፍልስፍና የሀገሪቱንና የሕዝቧን ፍላጎቶች ሲቦረቡሩ ቆይተዋል:: ይህ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን ማነቆ ሁኗል :: በልዩነቶች ላይ ማተኮር የሚረዳው ገዥውን ፓርቲ እንጅ ፥ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ አይደለም ::

ሦስት ምሳሌዎች ልስጥ :-

--- በተከታታይ የዓፄ ኃይለ ሥላሴንና የደርግን ሥርዓቶች እንዲሁም አሁን የወያኔን ሥርዓት ስንቃወም፥ የመጨረሻ ግባችንና መተኪያውስ ምንድን ነው? የሚለውን በጥሞና ያሰብንበት አይመስለኝም ::

----- በልዩነቶች ላይ ስላተኮርን ፥ ኢትዮጵያና ሕዝቧ የባህር በሩን አጥተዋል :: በመሆኑም የኢትዮጵያና የኤርትራ ወንድማማች ሕዝብ የጋራ ጥቅሙን ተነፍጓል :: ለዚህ የሚከፈለው የኢኮኖሚ ዋጋ ከፍተኛ ነው ::

---- በልዩነቶች ላይ ስላተኮርን ፥ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አውታሮች ለውጭ ሀገር መንግሥታትና ሐብታሞች እንዲሁም ለጥቂት የመንግሥት ደጋፊዎች እየተሰጡ ነው :: የመሬት ንጠቂያና ቅርምት ለዚህ ምሳሌ ነው ::

## ሐ. የሚመስለኝ መፍተሔው

በእኔ አመለካከት ለኢትዮጵያ አንድነትና ለሕዝቧ ዘላቂ ጥቅም አብሮ አለመቆም ፥ ለማነኛውም የተቀደሰ ዲሞክራሲያዊ ዓላማ ማነቆ ሁኗል ::

-----ካለፈው ስህተቶቻችን የምንማረው የማይካድ ትምህርት በጎሳና በሃይማኖት ወይንም

በርዕዮተ-ዓለም ልዩነቶች ላይ ያተኮረ የፖለቲካ ባህል ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያየለ መሆኑን ነው:: ዒላማው ጨቋኝና ከፋፋይ የሆነውን የወያኔ / ኢሕአደግ ሥርዓት/ መንግሥት አፍርሶ በምትኩ ለብሔራዊ አንድነት፥ ለነፃነት ፥ ለዕኩልነት ፥ ለፍትህ-ርትዕ፥ ለተሳታፊነት፥ ለሕግ የበላይነትና ለዲሞክራሲ ሥርዓት እጅና- ጓንት ሁኖ መስራት ነው ::

------ እኔ እንደማምነው ፥ 90 ሚሊዮን የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመኘውና የሚፈልገው ለዚህ መሪ ዓላማ ዕውን መሆን፥ የፖለቲካ ድርጅትና አመራር ብቁነት ነው:: የዓላማ አንድንት ከሌለ ይህ ብቁነት እውን አይሆንም :: ድኅነትን፥ ርሐብን፥ ጥገኝነትን፥ ሥራ አጥነትን፥ በሽታን ሙስናንና ዘረፋን ወዘተ..ለማጥፋት የሚቻለው፥ በአንድነት ታግሎ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመጎናፀፍ ሲቻል ነው :: አገር፥ የሕዝብ ህብረትና አንድነት ፍትኅ ርትዕ ከሌሉ የሁሉም ኑሮ ሊሻሻል አይችልም ::

--- ምርጫ ዘጠና ሰባትና ቅንጅት ለአንድነትና ለኅብረት ያደረገው ጥረት የሚያስተምረንም ይኸንኑ ነው እላለሁ ::

----- በአገር አንድነት፥ በሉዓላዊነትና በዕኩልነት ላይ የተገነባ ሥርዓት ዒላማ ካልሆነ፥ ዛሬ በግብፅ፥ ቱኒዥያ፥ ሊቢያ፥ ሶሪያና የመን የምናየው በወጣት ትውልድ የሚመራ አገር- ወለድ ሕዝባዊ አመፅ፥ በአገራችን እውን ይሆናል ብየ ለመገመት ያዳግተኛል:: ዕውን ካልሆነ ደግሞ፥ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ኑሮ ለአብዛኛው ሕዝብ አሁንም እንቆቅልሽ ሁኖ ይቆያል :: አብሮ መስራት ፥መተማመንና መከባበር ለዓላማ አንድነት ያለ ድብቅ አጀንዳ በገቢር ማሳየት ዘላቂና ብሩኅ ለውጥን እንደሚያመጣ አልጣራ ጠርም:: ለዚህ የሚበጀው፥በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የማያወላውል ዕምነት ሲኖር ብቻ ነው :: እኔ በበኩሌ ዕምነቴ የጠነከረ ነው ::

------- አንድአንድ የብሄር ነፃ አውጭ ግባሮችና መሰሎቻቸው፥ ሰብዓዊ መብትና ነፃነት እኩልነትና ፍትኅ-ርትዕ ከብሄራዊ አንድነትና ሉዓላዊነት ጋር አብረው አይሄዱም የሚሉት የተሳሳተ እሴት ለነፃነት አይበጅም :: እንዲያውም የነፃነታችንና እኩልነታችን መሠረት አንድነታችን ነው ::

------- <u>መነሻና</u> <u>መድረሻችን</u> ኢትዮጵያና የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘላቂ ጥቅም እስከ ሆነ ድረስ ፥ ዲሞክራሲያዊ ለውጥ መምጣቱ ምንም አያጠራጥረኝም :: አገር ከሌለ ግን ለዲሞክራሲ የሚደረገው ትግል ፋይዳ ሊኖረው አይችልም :: እንዲያውም ፥የገኘሁውን ፓርቲ ዕድሜ ያራዝማል ብል ከዕውነት የራቅሁ አይመስለኝም ::

------ በአጭሩ ፥በልዩነታችን ላይ የምናደርገው ትኩረት አገራችንን ለአደጋ ጥሏታል:: የሕዝባችን ነፃነትና ዕኩልነት ትግልን ጎድቷል፤ ወጣቱ ትውልድ ለአገርና ሕዝብ ጥቅም በአንድነት እንዳይቆም አርዓያ ነስቷል ፥ የሕዝብን የተቻችሎ መኖርን ባኅል ቦርቡሮታል ::ይህ ሁኔታ ከቀጠለ፥ የሶማሊያ ዕድል ወደ እኛ እንዳይዛመት እፈራለሁ::

## <u>መ/ ከኤኮኖሚው ጋር ያለው ግንኙነት</u>

አገር ከሌለ ዕድገት የለም:: ጥሩ አመራር ከሌለ አድሉአዊነት ይቀጥላል:: ዕጣችን ሆኖ፥ አሁንም፥ 4. 5 ሚሊዮን የሆኑ ወገኖቻችን፥ በሰው- ሰራሽ የረሐብ አለንጋ ይገረፋሉ:: ህፃ ናትና እናቶች በየቀኑ ይረግፋሉ:: የማን ልጅ ይሞታል ? የማን ልጅ እንደ ልቡ በልቶ ያድራል ? ብለን መጠይቅ አስፈላጊ ነው :: የ BBC ዘገባ የሚያሳየው፥ የህወሐት ኢሕአደግ መንግሥት፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የምግብ ዋስትና እንዲኖረው ለዕርሻው ክፍል ቅድሚያ አለመስጠቱን ጭምር ነው:: እንዲያውም፥ የምግብና ሌላ ዕርዳታን ለፖለቲካ ቁጥጥር እንደሚጠቀምበት ብዙ ማስረጃ ቀርቧል::

------ ይህ እየተመላለሰ የሚመጣ የርሃብ ቅጣት ብቻ ተቃዋሚ ኃየሎችን ነገ- ሰልስት ሳይሉ፥ ከላይ ለገለጽኩት ዓቢይ ዓላማ ከአንድ ላይ መቆም እንዳለባቸው ያሰምራል ።

/////////////////////////////-----------////////////////////////////////